# ጊንጥ

የመንደፈራ ሕዝብ በሩን ዘግቶ ከተኛ ሰዓታት አልፈዋል። ሌሊቱ በጨለማ መዋጥ ብቻ ሳይሆን« ደምፅ አታሰሙ»!!! የሚለው ትእዛዝ ለሰራዊቱም የደረሰ ይመስል ባካባቢው የነገሰውን ፀጥታ የሚያደፈርስ ነገር ቢኖር የ36 ወታደሮች ኮቴ ብቻ ነበር። አካባቢውን ስለሚያውቀው የሚገጥማን መተንበይ ስለማንችል ጉዞአችን በጥንቃቄ የተያዘ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ዛሬ ነፃ ወታደሮች ነን። አለቃና ታዛዥ ሚና ተሚነታችን ተሰርዟል። የጠላት ሃይል የቀኝ ጉብታውን ይዟል የወገን ጦር በስተቀኝ ተንቀሳቅሶ ሁለተኛ የመቶ በስተግራ ያቀናና ጥቃት ይፈፅማል፤ የአንደኛ የመቶ ከመሃል ያለውን ገዥ መሬት ይዞ ሽፋን ይሰጣል። የሚል አለቃ የለንም። የጠላት ጦር የስንቅ እጥረት አለበት፣ ትጥቁ በነፍስ ወከፍ ከመቶ ያልበለጠ ጥይትና፣ ሁለት ቦምብ ነው። ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት በጣም የላላና በፍርሃት ላይ የተመሰረተ ነው፤ የውጊያ ብቃቱ ያልተፈተነ፣ ከተአለም (ከማሰልጠኛ ጣቢያ) የወጣ ነው። የወገስ ጦር እንደምታዩት በትጥቅ የተሟላና በውጊያ ብቃቱም ተወዳዳሪ የሌለው በተመክሮውም የሚኮራ ስለሆነ የሚበግረው ምንም ነገር አይኖርም ብሎ የሚያበረታታን፣ ብሎም አቅጣጫ የሚመራን፣ በአሸዋ ገበታ ላይ የአካባቢውን አቀማመጥ የሚያሳየን አዋጊ መኮንን በአጠገባችን የለም።

ዛሪ ሁላችንም የወሳኔው ተካፋዮች ነን።ዛሬ የትላንት ወታደሮች ሳንሆን እምቢ አሻፈረን ያልን አማጽያን ተጋዳዮች ሆነናል። ከሕዝቡ ጎን እንቆማለን ስንል አባባላችን ወሸት እንዳልነበረ ላላመኑን ለሚያረጋግጥ ሳይሆን ላመንበት ልንሰዋ የቆረጥን ከትግሉ ለመቀላቀል የምናኮበኩብ የሕዝብ ነብሮች ነን። መዝሙራችን ሚዜክራችን ሁሉ ተቀይሮ ከሰፊው ሕዝብ ትግል ልንቀላቀል የመጀመሪያውን እርምጃ ከጀመርን ሰዓታት አለፉ። ጥለንው የወጣነው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግቢ ከዐይናችን የተሰወረው ገና የመንደፈራን ከተማ እንደለቀቅን ነበር። አካባቢውን ከቦ ያለው የ10ኛ ሻለቃ ጦር በሁኔታው መደናገጥ ብቻ ሳይሆን ምን እየተደረገ ነው የሚለውን የሰማው ከመሃከላችን እየሾለኩ ከተቀላቀሉት ወታደሮች ነው። «አየር ወለዶች እየከዱ ነው» የሚለው ወሬ ሁሉንም በጥብጦታል። ወንደሞቻችን ናቸው ተዋጉ ብንባልም አንዋጋም ከሚለውና ወንበዴ አወናብዷቸዋል ብሎ ከሚከራከረው ጭምር በሰራዊቱ መካከል ትልቅ ወዥንብር ተፈጥሯል። ትላንት አየር ወለድን ይመራ የነበረው ኮሎኔል ዛሬ መኣረጉን ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ላመነበት አላማ ለሰዋ ለማሳቱ ምክር አስፈላጊ አልነበረም። ቢሆንም አሁንም ግርማ ሞገሱ ግን እንዳለ ነው። ዛሬ ኮሎኔል ብሎ የሚጠራው አብሮት ያመፀው ወታደር አጠራሩ አሰባሳቢዬ አባቴ እንደማለት ያስመስልበት ነበር። ከራሳችን ይልቅ እሱን ከመሃል አስገብተን ስንቀሳቀስ ኮሎኔሉን ለመያዝ ደርግ የተቻለውን ጥረት ማድረጉ እንደማይቀር ለሁላችንም የአደባባይ ሚስጥር ስለነበረ ጭምር ነው።

ከመንደፈራ ከወጣን ሰዓታት አልፈዋል። አልፎ አልፎ የጥይት ተኩስ እንሰማለን። እኛን የሚያሰጋን አልነበረም። አሁን ወደ ቀተ ሌሊት እየሆነ ስለሆነ የአወሮፕላን

ፍራቻ የለብንም ። ይህንን እንቅስቃሴ የሚመራው በመሃከላችን የተቋቋመው ኮሚቴ ሁሉም ነገር ስነስርአት በተሞላበት ማንገድ መካሄድ እንዳለበት ሲያሳስብ ቅጽበታዊ ውሳኔ ሲያደርግ እንደትላንቱ በቅደሚያ ተዋረድ ሳይሆን ለተወሰኑ ግለሰቦች ሙሉ ስልጣን ተሰጥቶ ነበር።

ዛሬ ለነገ የሚሆን ስንቅ የለንም ። እያንዳንዳችን ያነገብነው M14 ጠበመንጃ ቢያንስ ለቀናት ሊያወለን ከሚችል ጥይት ጋር ከደረታችን ላይ ደግሞ ግራና ቀኝ የተንጠለጠለው የእጅ ቦምብ የልብ ልብ እንደሰጠን መናገር ግን እውነት ነው ። ከሕዝብ ጋር እንሰለፋለን ጥቂት የወታደር ተመራጮች የሚመሩት አንባ ገነን ወታደራዊ ስርአት ሳይሆን የሕዝብ ተሳትፎ ያለበት በምርጫ ዲሞክራሲ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መፍጠር አማራጭ የሌለው ነው ብለን ከተቀበልን ሰነበተ። ለዚህም ዓላማ መሳሳታችንን ለማስየት ከአስመራው የሁለተኛ ክፍለ ጦር አባላት ጋር ግልጽ ውይይት በማድረግ ቅስቀሳ ማካሄዳችን፣ ብሎም በጊዜው የክፍለ ሃገሩ አስተዳዳሪ የነበሩትን ጀነራል ጌታቸው ናደውን በይፋ ፊት ለፊት መጋተራችን ጥምር አብሮ የሚከተት ነው ።

መዘሙራችን
ሰላም ይላችኋል ከአየር ላይ ወርዶ፣
ያየር ወለዳችሁ የፓራ ኮማንዶ። ማለት ቀርቶ

ግፍን ተቃወሜ ጭቆናን ፈርቼ፣
መሄዴ ነው ጫካ መሄዴ ነው ደን፣
ላርሶ አደሩ ለላብ አደሩ ልሆነው መከታ ልሆነው ተገን።
የሚል ሆኗል።

ዛሬ እንደትላንትናው ተነሱ ግዳጅ አለ የሚለን የለም ። ግዳጃችን ከሕዝቡ ጎን መሰለፍ ብቻ ነበር። ዛሬ ሌሎች በቀየሱት ሌሎች በተስማሙበት በማናውቀውና በማናምንበት ጦርነት መማገድ የለም ። ለመሰዋት የተነሳነው ለምናውቀውና ለምናምንበት ዓላማ ብቻ ነው ። የምንተነፍሰው አየር በጥንቀት ሳይሆን ነፃነት የሰፈነበት መሆኑን ስናስብ ደስታ ይዞን እንደእንቦሳ ፈንጥዞ ያሰኘናል። ጉዞአችን ወጣ ወረድ የሞላበት አደካሚ እረጅም እንደሚሆን ደግሞ አስተዋሽ የሚያስፈልገን አልነበርን። የነገው ብሩህ ተስፋ ግን እንደአወሎ ነፋስ ወደፊት ያንደረደረን ነበር።

«ሶፍራ ያዝ» አለ ከአስተባባሪዎቹ አንዱ ። ሁሉም እንደ ጤፍ ዘር በአንድ ጊዜ ብትን ብሎ ምሽግ ሊሆነው የሚችለውን ድንጋይና ቁጥቋጦ ስር ተንፈራጠጠ ። ደርግ ደረሰብን ማለት ነው አልን። ትላንት ጎን ለጎን ከተሰለፍነው ወታደሮች ጋር ዛሬ በተፃራሪ ሆነን ልንዋጋ ነው ። በዚያን ወቅት በንፋስ እየተገፋ የሚንከባለልን ቅጠል የጠለት ኮቴ ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ወይም ፈሪነት አልነበረም ። ንፋሱ እየተንሾካሾኩ የሚያወሩ ሰዎች በአጠገብ እንዳሉ ያህል ስለሚያስመስል ለምን ተኩስ አንባልም እያሉ የተቁነጠነጡ ብዙዎች ነበሩ። ትእዛዝ ያስተላለፈው አስተባባሪ ከፊት ያለውን ቃፊር ከጉብታው አናት ላይ እንዲቆይ መመሪያ ሰጥቶ ሲመለስ በትንሹ ይሰማ የነበረው ጩኸት እየጠነከረ መጣ ።

እያነቅከኝ እኮነው አለው። ፍርሃት ይዞት በቀኝ እጁ አንገቱላይ የተጠማጠመውን ጠንቻ ለማስለቀቅ እየሞከረ። አጠገቡ የነበረ ሌላ ወታደር በሁኔታው ተደናግጦ አርፈህ ተቀመጥ ያለው

